# ፕሮስፔክተስ

## ዳሎል ኦይል አ.ማ.

DALOL

**ዳሎል ኦይል አ.ማ.**

<u>በታሳቢነት ለተያዘ ሰው ብቻ የሚሰጥ</u>

# ማ ው ጫ


1 የአደራጆች መልዕክት

2 ስለ አክስዮን ሽያጭ ጠቅለል ያለ መረጃ

3 የአደራጆች ማንነት መግለጫ

10 የኢትዮጵያ የነዳጅ ኢንዱስትሪ ቅኝት

11 ስለ ዳሎል አይል አ.ማ. አጭር መግለጫ

12 በዳሎል አይል አ.ማ. ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉባቸው  አምስት ምክንያቶች

15 ክፍል ሀ- ህግ ነክ መረጃዎች

ምሥረታ እና ምዝገባ

የኩባንያው ዓላማዎች

አወቃቀር እና አመራር

የትርፍ አከፋፈል

የአክስዮን ሽያጭ

17 ክፍል ለ- ተጨማሪ መረጃዎች

የመመስረቻ ፅሁፍ ማጠቃለያ

የመተዳደሪያ ደንብ ማጠቃለያ

ሂሣብ የተከፈተባቸው ባንኮች ዝርዝር

የግለሰብ/የድርጅት የማመልከቻ ፎርም

# ዳሎል ኦይል አ.ማ.

## የአደራጆች መልዕክት

ኢትዮጵያ ላለፉት ተከታታይ ዓመታት በተደጋጋሚ ባለሁለት አሀዝ ምጣኔያዊ ዕድገት በማስመዝገብ ፈጣን የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት በማሣየት ላይ ትገኛለች። የኢኮኖሚ ዕድገቱ ቀጣይነት ቁልፍ በሆኑ የፍጆታ አመላካቾች በሆኑት እንደ ሀይል፣ ኢነርጂ፣ ሲሚንቶ በመሳሰሉት ላይ ይታያል። እነደ ቤንዚን፣ ናፍጣ እና ነጭ ጋዝ የመሳሰሉት የነዳጅ ምርቶች ተጠቃሚነት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ ሲሆን ዕድገቱ በየዓመቱ አስር በመቶ እየጨመረ ይገኛል። ባለፉት ሦስት ዓመታት የነዳጅ፣ ቅባቶችና ዘይቶች ተጠቃሚነትም ባለ ሁለት አሀዝ እድገት አሣይቷል። በተጨማሪም ነዳጅ የግድ ተፈላጊ ምርት በመሆኑና ተፈላጊነቱም የማይዋዥቅ ስለሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት በሚቀንስበት ጊዜ እንኳን ቢሆን ተፈላጊነቱ በቀጣይነት ይጨምራል።

ረዘም ላሉ አመታት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄደውን የተጠቃሚውን የነዳጅ ምርት ፍላጎት ከማርካት ረገድ ይህ ነው የሚባል ውድድር የማያደርጉ ጥቂት አለምአቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች የነዳጅ ኢንዱስትሪውን በበላይነት ይቆጣጠሩት ነበር። ቀጣይነት ካለውና እያደገ በመሄድ ላይ ከሚገኘው የነዳጅ ምርቶች ተፈላጊነት አኳያ በሥራ ላይ ባሉት የነዳጅ ኩባንያዎች የሚደረገው አቅርቦትና የአገልግሎት መስፋፋት ዘገምተኛ ነው። በተጨማሪም አለምአቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከገበያ መውጣታቸው የነዳጅ ኢንዱስትሪው በሀገሪቱ እየጨመረ ላለው የነዳጅ ምርቶች ፍላጎትን የማሟላት አቅሙን አዳክሞታል።

ዳሎል ኦይል አክሲዮን ማህበር በነዳጅ ኢንዱስትሪው የዳበረ የሀገር ውስጥ እና አለም አቀፍ ልምድ ባላቸው እና ሀገር በቀል የሆነ ብልፅግናን ለመፍጠርና ለማጠናከር ቆርጠው በተነሱ ኢትዮጵያውያን የተመሠረተ ኩባንያ ነው። የዳሎል ኦይል አ.ማ. እየጨመረ በመሄድ ላይ ያለውን የሀገራችንን የነዳጅ ምርቶችና አገልግሎቶች ፍላጎትን ለማርካት እና ባለሀብቶች ለሚያፈሱት ሀብት አስተማማኝ እና ማራኪ የሆነ ትርፍ ማስገኘትን ዋና ዓላማው አድርጎ ተነስቷል።

የዳሎል ኦይል አክስዮን ማህበር አደራጅ የሆነው ስኬት ኘሮሞሽን ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በበኩሉ እየጨመረ በመሄድ ላይ ያለውን የሀገራችንን የኢነርጂ ሴክተር ፍላጎት የሚሟላት አቅምን የሚያጎለብት ከከፍተኛ ትርፍ ጋር ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ይህንን የኢንቨስትመንት ዕድል ለህዝብ ሲያቀርብ ከፍተኛ ኩራትና ደስታ ይሰማዋል። የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን እና የውጭ ባለሀብቶች አክስዮኖች ላይ ኢንቨስት በማድረግ ፣ ሀገር በቀል የሆነ ከፍተኛ የሥራ ዕድል የሚፈጥር እና ለትውልድ የሚተላለፍ ፣ዕድሜ ልክ ትርፋማ የሚሆን የነዳጅ ኩባንያ እውን የማድረግ ራዕያችን ተካፋይ እንድትሆኑ በማክበር እንጋብዛለን።

አቶ ኢዲዲያ አሰፋ
ዋና ሥራ አስኪያጅ
ስኬት ኘሮሞሽን ኃ.የተ.የግ.ማ.

## ስለአክስዮን ሽያጭ ጠቅለል ያለ መረጃ
## ዳሎል ኦይል አክስዮን ማህበር

150,000 የተመዘገቡ መደበኛ አክስዮኖችን ለህዝብ ሽያጭ አቅርቧል።

| | |
|---|---|
| የአንድ አክስዮን ፓር ቫልዮ | ብር 1,000 |
| የአንድ አክስዮን መሸጫ ዋጋ | ብር 1,000 |
| ለአንድ አክስዮን የሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ | ብር 70 (7%) |

አንድ መቶ እና ከዚያ በላይ የሆኑ አክስዮኖች ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉ እና ሙሉ ክፍያውን እስከ ጥቅምት 21 ቀን 2002 ዓ.ም. የሚፈፅሙ የሁሉ የዳሎል አይል አክስዮን ማህበር ነዳጅ ማደያና አገልግሎት መስጫ ጣብያዎች ዲለር (ወኪል) የመሆን እድል ይኖራቸዋል።

| | |
|---|---|
| የአከፋፈል ሁኔታ | 30% በምዝገባ ጊዜ |
| | 40% እስከ የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም. |
| | 30% እስከ ነሐሴ 25 ቀን 2002 ዓ.ም. |

<u>ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች</u>

ዝቅተኛ ኢንቨስትመንት 10 አክስዮኖች (ብር 10,700)
ከፍተኛ ኢንቨስትመንት 20% ወይም 30,000 አክስዮኖች (ብር 32.1 ሚልዬን)

<u>ትውልደ ኢትዮጵያውያን ላልሆኑ የውጭ ዜጎች</u>

ከሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር በሽርክና ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን 60,000 የአሜሪካ ዶላር ነው።

ሽያጭ የተጀመረበት ቀን ፡- ነሐሴ 26 ቀን 2001 ዓ.ም.
ሽያጭ የሚያበቃበት ቀን ፡- ታህሣስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም.

<u>አ ድ ራ ሻ</u>

ዳሎል አይል አክስዮን ማህበር
ፖ.ሣ.ቁ. 11937
ኢትዮ - ቻይና ወዳጅነት መንገድ (ወሎ ሰፈር)
ሜድኮ ባዮ ሜዲካል ኮሌጅ አጠገብ የሚገኘው አዲስ ህንፃ ሁለተኛ ፎቅ
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ስ.ቁ. + 25111 416 38 38 ፤ +2511 416 57 57
+ 25111 416 17 32 ፤ +2511 416 17 33
ፋክስ + 25111416 40 02
ኢ.ሜል፡- info@daloloil.com
ድህረ ገፅ፡- www. daloloil.com

# ስለ አደራጆች መግለጫ



አቶ ኢዲዲያ አሰፋ
የዳሎል አይል አክስዮን ማህበር ዋና ስራ አስፈፃሚ እና ዋና አደራጅ

አቶ ኢዲዲያ አሰፋ የዳሎል አይል አ.ማ. ዋና ስራ አስፈፃሚ እና ዋና አደራጅ ናቸው። አቶ ኢዲዲያ በንግድ አስተዳደር የማስትሬት ዲግሪያቸውን ስኮትላንድ ከሚገኘው ኤዲንበርግ ቢዝነስ ስኩል ያገኙ ሲሆን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በማኔጅመንት እና ፐብሊክ አድሚኒስትሬሽን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል። ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ በሼል ኩባንያ ውስጥ ከ10 ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ፣አፍሪካና የእስያ ፓስፊክ ሀገራት በተለያዩ የሀላፊነት ዘርፎች አገልግለዋል።

አቶ ኢዲዲያ የአዲስ አበባ፣ ሰሜን፣ ምዕራብና ደቡብ ኢትዮጵያ ክፍሎች የሽያጭ ተጠሪ በመሆን በሀገሪቱ የሚገኙትን የሼል ማደያ ጣብያዎች አገልግሎት አሰጣጥን በመምራት ሰርተዋል። ቀጥሎም የሪቴይል ኔትዎርክ ዴቪሎፕመንት ስራ አስኪያጅ በመሆን የኩባንያውን የቸርቻሮ መረብ ብቃት ባለው ሁኔታ ነዳጅ ማደያዎችን የማስፋፋትና የማጠፍ ክንውን ሀላፊነታቸውን ተወጥተዋል። አቶ ኢዲዲያ ለሼል ኢትዮጵያ የአቅጣጫ ጠቋሚ በመሆን ያገለገሉና ኩባንያው በቁልፍ ስትራቴጂያዊ በሆኑ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ላይ ማደያዎች እንዲከፍት እና ትርፋማ ባልሆኑ ቦታዎች ላይ የተከፈቱት እንዲቀነሱ ለማድረግ ያስቻለ የአምስት አመት የቸርቻሮ መረብ ማስተር ፕላን በማዘጋጀት የሚጠቀስ ስራ ሰርተዋል። እ.ኤ.አ. በ2003 ዓ.ም አቶ አዲዲያ ወደ ማሌይዥያ ተልከው ለሼል ማሌዥያና ሲንጋፖር ብራንድ ማኔጀር በመሆን አገልግለዋል። በተሰጣቸው ሀላፊነትም የሼል አርማዎች ጠባቂ በመሆን አለም አቀፍ እውቅና ካላቸው እንደ (J. Walter Thomson) ፣ (one 4 one) እና ሌሎች አለም አቀፍ የብራንድ እና የማስታወቂያ ድርጅቶች ጋር በቅርበት ሰርተዋል። በማይሌዥያ ቆይታቸው የሎያሊቲ ማርኬቲንግ ስራ አስኪያጅ በመሆን ከአራት ሚሊዮን በላይ አባላት ያሉት ቦነስ ሊንክ ተብሎ የሚጠራ የሼል ሎያሊቲ ፕሮግራምን በሀላፊነት መርተዋል።

ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ በሼል አይል ፕሮዳክትስ አፍሪካ (Shell Oil Products Afica) ለምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ አፍሪካ ማለትም ኢትዮጵያ ፣ ኡጋንዳ ፣ ኬንያ ፣ ሱዳን ፣ ግብፅ ፣ ሞሪሺየስ ፣ ማዳጋስካር፣ ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ቦትስዋና እና ናሚቢያን በመሸፈን የክፍለ አህጉሩ የስልጠና ስራ አስኪያጅ በመሆን አገልግለዋል። በዚህ ሚናቸው በአፍሪካን እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚሰሩ የሼል ኩባንያዎች ጋር በመስራት በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ስላለው የነዳጅ ንግድ ሥራ ከፍተኛ ልምድ ቀስመዋል። ሼል ኢትዮጵያ በአይል ሊቢያ ሆልዲንግስ ሊሚትድ ከተገዛ በኋላ የሪቴይል ስራ አስኪያጅ በመሆን ኩባንያው በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የቸርቻሮ ሥራዎችን በተመለከተ በሀላፊነት አገልግለዋል። አቶ ኢዲዲያ በሥራ አመራር እና የመሪነት ክህሎት ማዳበር የሚሰራ እና ሥልጠናዎችን፣ አመራሮችንና የምክር አገልግሎትን በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጪ የሚሰጥ ሴንተር ፎር አፍሪካን ሊደርሺፕ ዲቨሎፕመንት (ካልድ) የተባለ ምክር ሰጪ ተቋም መስራች ናቸው።



አቶ ፍስሀ አስረስ
ተባባሪ አደራጅ እና የዳሎል አይል አ.ማ. የቦርድ አባል

አቶ ፍሰሀ አስረስ የኢንተርኮንቲኔንታል አዲስ ሆቴል ዋና ስራ አስኪያጅ ናቸው። በኔዘርላድስ ከሚገኘው ኢንስቲትዮት አፍ ሶሻል ስተዲይስ በሥራ አመራር የማስተሬት ዲግሪ፣ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥራ አመራር እና ህዝብ አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝተዋል። አቶ ፍሰሀ በረዳት ምሩቅነት በማስተማር፣በምርምር እና ምክር አገልግሎት ዘርፍ በወቅቱ የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ተብሎ ይጠራ በነበረው መስሪያ ቤት ሰርተዋል።

ከ1982 እስከ ጥቅምት 1992 ዓ.ም. ድረስ በሼል ኢትዮጵያ ሊሚትድ ሰርተዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ በሪቴይል፣ ደንበኞች አገልግሎት ፣ ኮሜርሻል እና የአየር መጓጓዣ ነዳጅ ሽያጭ ክፍሎች ውስጥ በሃላፊነት ሰርተዋል። ከሼል ጋር ይሰሩ በነበሩበት ወቅት “በአዳይ ባለቤትነት የሚሰሩ ማደያዎች” (Dealer Owned) በሚል አዲስ አሰራር በርካታ የነዳጅ ማደያዎች ተከፍተዋል። አቶ ፍሰሀ ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት ጋር በፈጠሩት መልካም የሥራ ግንኙነት አማካኝነት ለኩባንያው በርካታ የሥራ እድሎች ፈጥረውለታል።

አቶ ፍስሀ ከጥቅምት 1992 ዓ.ም. ጀምሮ በሂልተን ኢንተርናሽናል ሆቴል የሰው ሀይል ስራ አስኪያጅ በመሆን ያገለገሉ ሲሆን በዚህ ወቅት በአቶ ፍስሀ አነሣሽነት ሆቴሉን ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ እና የሰው ሀይሉን የሚያጠናክሩ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። ከጊዜ በኋላም የሆቴሉ የፍሮንት ኦፊስ ኦፕሬሽን ስራ አስኪያጅ ሆነው የተሾሙ ሲሆን በአዲሱ ኢንተርኮንቲነንታል አዲስ ሆቴል ስራቸውን እስከጀመሩበት እስከ ሰኔ 2000 ዓ.ም. ድረስ በዚሁ የሀላፊነት ስራ አገልግለዋል። አቶ ፍስሀ ሂልተን ሆቴል በቆዩበት ወቅት የሆቴሉ ክፍሎች 90% ያህል ድረስ ይያዙ የነበረ ሲሆን ሆቴሉም በማህበረሰቡ ዘንድ ተመራጭ ሆኗል። ለዚህም አቶ ፍስሀ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

በ2000 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ አቶ ፍስሀ አሁን ያሉበትን የኢንተር ኮንቲኔንታል አዲስ ዋና ስራ አስኪያጅነት ስራ የጀመሩ ሲሆን ይህም የመጀመሪያው የባለ አምስት ኮከብ ሆቴል ኢትዮጵያዊ ስራ አስኪያጅ አድርጓቸዋል። ሆቴሉን ከጅምሩ ያደራጁት ሲሆን ከኢትዮጵያዊ ቡድን ጋር በመሆን ፈታኝ ነገር ግን የተሣካ የሆቴሉን የቅድመ መክፈቻና የታላቅ መክፍቻ የምርቃት በዓሎችን አዘጋጅተዋል። በአሁኑ ወቅት ሆቴሉ በኢትዮጵያውያን እና የውጭ እንግዶች ተፈላጊ የሆነና የከተማችን ደማቅ መናኸሪያ ሆኗል።

አቶ ፍስሀ ከኢትዮ-ፓረንትስ ትምህርት ቤት መሥራቾች አንዱ ከመሆናቸው በተጨማሪ ትምህርት ቤቱን በቦርድ አባልነትና በቢዝነስ ዴቨሎፕመንት ኮሚቴ አባልነት ለስድስት ዓመታት ያህል አገልግለዋል። በተጨማሪም የኢሌጋንት ኋ.የተ.የግል ማህበር የቦርድ ሊቀመንበር በመሆን ለስድስት ዓመት፤ የሲስቴክ ኋ.የተ.የግ.ማህበር እና የቡራዩ ወረቀትና ፓኬጂንግ ኋ.የተ.የግ.ማህበር የቦርድ አባል በመሆን ከስምንት ዓመታት በላይ አገልግለዋል። ሶረኔ ቢዝነስ ግሩፕን በማቋቋምና በማደራጀት የተሣተፉ ሲሆን የንግዱ ባለቤት ልዩ አማካሪ በመሆን ከአስር ዓመት በላይ አገልግለዋል።

# ስለ አደራጆች መግለጫ



ኢንጂነር ደረጀ ዋለልኝ
የዳሎል አይል አ.ማ ተባባሪ አደራጅ እና የቦርድ አባል

ኢንጂነር ደረጀ ዋለልኝ ሪኒወብል ኢነርጂ ላይ የተሰማራው የሊደትኮ ኋ.የተ.የግ.ማህበር ባለቤትና ማኔጂንግ ዳይሬክተር፣ መሠረታዊ ቅባቶችን በመጭመቅ ላይ የተሰማራው የአበሻ ቃና ትሬድ ኤንድ ኢንዱስትሪ ኋ.የተ.የግ.ማ. ማኔጂንግ ዳይሬክተር እና በአሁኑ ወቅት ደግሞ ባለቤትና የኢትዮጵያ የፀሀይ (Solar) ኢነርጂ ማህበር ፕሬዚዳንት ናቸው። ኢንጂነር ደረጀ የባችለር ኦፍ ሣይንስ ዲግሪያቸውን በሲቪል ምህንድስና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ፋክልቲ በ1974 ዓ.ም. አግኝተዋል።

ኢንጂነር ደረጀ ስራ የጀመሩት በቀድሞ የኢትዮጵያ ህንፃ ኮንስትራክሽን ውስጥ የሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ ፋብሪካ በሣይት ኢንጂነርነት ሲሆን በኋላም በጅማ ጤና ሣይንስ ኢንስቲትዮት ግንባታ ወቅት በፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅነት ሰርተዋል። የጅማ ጤና ሣይንስ ተቋም ግንባታ ተማሪዎችን ለመቀበል ከነበረው ዕቅድ አኳያ ወደ ኋላ ቀርቶ የነበረ ሲሆን በኢንጅነር ደረጀ ብቃትና የላቀ ጥረት አብዛኛው የግንባታ ስራ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ሊጠናቀቅ የቻለ ሲሆን በዚሁም የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ በመሆን ተሹመዋል።

ኢንጂነር ደረጀ በ1980 ዓ.ም. ሼል ኢትዮጵያ ሊሚትድ የገቡ ሲሆን የተለያዩ የምህንድስና ስራዎችን በመስራት በኩባንያው  ለ12 ዓመታት ያህል አገልግለዋል። በሼል በነበሩበት ወቅት በፕሮጀክት መሀንዲስነት፣ በቁሣቁስ መሀንዲስነት፣ ለአሰብ ኢንስታሌሽን በኦፐሬሽን ረዳትነት ያገለገሉ ሲሆን በመጨረሻም የሼል ኢትዮጵያ፣ ሼል ኤርትራ እና ሼል ጅቡቲ የምህንድስና ሥራ አስኪያጅ በመሆን አገልግለዋል። የፕሮጀክት መሀንዲስ ሆነው በሰሩባቸው ጊዜያት ኢንጀነር ደረጀ በመላ ሀገሪቱ ለሚሰሩ የነዳጅ ዴፓዎች ዲዛይንና የነዳጅ ማደያ ጣብያዎች ግንባታ የምህንድስና ስራዎች ሀላፊ ነበሩ። ለጋዝ ሲሊንደሮች መሙያዎችን ጨምሮ፣ ለቡታጋዝ ፣ፓምፖች ወዘተ የኮንቬየር ቤልት ዘዴዎችን በመገንባትና በመትከል ሥራዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ክህሎታቸውን አሣይተዋል። የኦፕሬሽን ረዳት በነበሩበት ወቅት አሰብ ከነበረው የሼል ኢንስታሌሽን ወደ መላው የሀገራችን ክፍሎች የነዳጅ ምርቶችን በማስጫን ሀላፊነት ሰርተዋል። አሰብ የሰሩዋቸው ስራዎች የአውሮፕላን ነዳጅ ጥራትን ማረጋገጥ (በመላ ኢትዮጵያ አየር ማረፊያዎች የሚገኙ የነዳጅ ማደያዎች ደህንነትን ይጨምራል) እና ከነዳጅ አጓጓዥ መርከቦች ላይ የነዳጅ ምርቶችን ማራገፍ የሚያካትቱ ሲሆን ይህ ስራ ከሀገር ውጪ ስለሚደረግ የነደጅ ማጓጓዝ ያላቸውን እውቀት ለማዳበር ዕድል ሰጥቷቸዋል።

የችርቻሮ መሐንዲስ ሆነው ባገለገሉበት ወቅት ኢንጂነር ደረጀ እና የቡድን ጓደኞቻቸው በወቅቱ አዲስ የነበረውን ሪቴይል ቪዠዋል አይደንቲቲ በኢትዮጵያ በብቃትና ጊዜውን በጠበቀ ሁኔታ በመተግበራቸው ለሽልማት በቅተዋል። የምህንድስና ስራ አስኪያጅ በነበሩበት ወቅት ያከናወኑዋቸው በርካታ ተግባራት ውስጥ የጅቡቲን የችርቻሮ መረብ ማሣደግ፣ የግርድፍ አስፋልት ማከማቻ ታንክ ማሻሻል፣ የጅቡቲ ዴፓዎች ላይ የተለያዩ ለውጦችን ማድረግ በአሰብ ኢንስታሌሽን ላይ ያደረጉዋቸው የማሻሻያ ስራዎች ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው።



ኢንጂነር ነብያት ገዛኸኝ
የዳሎል አይል አክስዮን ማህበር ተባባሪ አደራጅ እና የቦርድ አባል

ኢንጂነር ነብያት ገዛኸኝ የዳሎል አይል አክስዮን ማህበር መስራች አባልና ተባባሪ አደራጅ ናቸው። በሜካኒካል ኢንጂኔሪንግ የመጀመሪያ ዲግሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል። ሥራ የጀመሩት በስኳር ኢንዱስትሪ ውስጥ በቴክኒክ ተቆጣጣሪነት ነበር። በሥራው በነበሩበት ወቅት አዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶችን የመሩ ሲሆን የምህንድስና እውቀታቸውንም በዚሁ ወቅት የበለጠ አዳብረዋል።

በ1987 ዓ.ም. የኤክሶን ሞቢል አካል በነበረው ሞቢል ኦይል ኢስት አፍሪካ ውስጥ በተለያዩ የሥራ መደቦች አገልግለዋል። ስለ ነዳጅ ኢንዱስትሪው የገበያ፣ የምህንድስና፣ የደህንነትና የአካባቢ ጥበቃን ያቀፈ ጥልቀት ያለው ተጨባጭ የሥራ ልምድ አዳብረዋል።

በኩባንያው ውስጥ በሽያጭ ኃላፊነት የሰሩ ሲሆን የነዳጅ ምርቶች በተለይም የዘይትና የቅባት ምርቶችን በመሸጥ ሃላፊነት ሥራ ላይ አገልግለዋል። የንግድ ሥራ ቀጣይነትን ማረጋገጥና አዳዲስ አሰራሮችን መቀየስ በዋናነት ትኩረት ሰጥተዋቸው ያከናውኑዋቸው የነበሩ ተግባራት ናቸው። በቀጣይነትም የዘይትና ቅባት ምርቶች ጥራት ተቆጣጣሪነት የሥራ መደብ እድገት አግኝተው በኃላፊነት ሰርተዋል። የኩባንያውን የሽያጭ መጠን በማሻሻል እና ትርፋማነቱን በመጨመር እንዲሁም ኩባንያውን ቀዳሚ ተወዳዳሪ በማድረግ ረገድ ላደረጉት የላቀ አስተዋፅኦ ምስጋና ተለግሷቸዋል። ሞቢል ኦይል ኢስት አፍሪካ (ኢትዮጵያን) በ1997 ዓ.ም. ቶታል ሲገዛው እሣቸውም ወደ ቶታል ኢትዮጵያ በመዛወር በተለያዩ የሥራ መደቦች አገልግለዋል። በመጀመሪያ የጤና ደህንነት እና የአካባቢ ጥበቃ አማካሪነት ከዚያም ወደ ምህንድስና ክፍል ተዛውረው የሪብራንዲንግ ፕሮጀክት ምክትል ስራ አስኪያጅ በመሆን አገልግለዋል። ከዚያም ወደ ሽያጭ ክፍል ተዛውረው የቴክኒካል አገልግሎት ስራ አስኪያጅ በመሆን አገልግለዋል።

ከ2000 ዓ.ም. ጀምረው ከቶታል ተሰናብተው ወደ አሜሪካን ሀገር የሄዱ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በዌስታት ኮርፓሬሽን እየሰሩ በፕሮጀክት አመራር የማስትሬት ዲግሪ ትምህርት በሜሪላንድ ዩኒቨርስቲ በመከታተል ላይ ይገኛሉ። ኢንጂነር ነብያት ዳሎል ኦይል አክስዮን ማህበርን በአሜሪካ ለሚገኙ ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ዘንድ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ናቸው።

## ስለ አደራጆች መግለጫ



ኘርፌሰር ባደግ በቀለ
የዳሎል አይል ኢ.ማ ተባባሪ አደራጅ እና የቦርድ ሊቀመንበር

ኘሮፌሰር ባደግ በቀለ የስኬታማው እና የከፍተኛ ትምህርት ዲግሪዎች ማለትም ኤም.ቢ.ኤ በኢንተርናሽናል ቢዝነስ፣ ኤም.ቢ.ኤ እና ኤም.ኤ በትራንስፎርሜሽናል ሊደርሸፕ የሚሰጠው የኢንተርናሽናል ሊደረሺፕ ኢንስቲትዩት መስራች፣ ባለቤትና ፕሬዘዳንት ናቸው። ኢንስቲትዮቱ በኦርጋናይዜሽናል ማኔጀመት፣ ቢዝነስ ማኔጅመንት፣ ኢኮኖሚክስ እና ኮሚኒቲ ዴቨሎኘመንት የትምህርት ዘርፎች በመጀመሪያ ዲግሪ ያስተምራል። በተለያዩ የመሪነት ርዕሶችም በመላ ኢትዮጵያ እና በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የአጭር ጊዜ ስልጠና ይሰጣል። ኘሮፌሰር ባደግ የታወቁ መምህር፣ የጉባኤ ንግግር አቅራቢ፣ ውጤታማ አመራርና አተገባበርን እና የሰው ሀይል አእምሮአዊ ሀብትን በማሣደግ ኢትዮጵያን ለመለወጥ ባላቸው ቁርጠኛ ፍላጎት ይታወቃሉ።

ለሀገራቸው ዕድገት ያላቸው ቀናነት ከረጅም ዓመታት የአሜሪካ ቆይታ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው እያከናወኑዋቸው ያሉት ስራዎችና እያቋቆሙዋቸው ያሉት ተቋማት ምስክሮች ናቸው። ካከናወኑዋቸው ተግባራት መካከል ኮንቲኔንታል ኒው ላይፍ ኢንተርናሽናል የተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት በአሜሪካ ያቋቋሙ ሲሆን ድርጅቱ በአዲስ አበባ ከተማ የጤና ማዕከል እንዲከፈት ድጋፍ አድርጓል። የጤና ማዕከሉ በአሁኑ ወቅት በየቀኑ ከ300 በላይ ለሚሆኑ ታካሚዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። በርካታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመላ ኢትዮጵያ አሰርተዋል። ከአሜርካ ሶሣይቲ ኦፍ ካታራክት ኤንድ ሪፍራክቲቭ ሰርጀሪ (ኤ.ኤስ.ሲ፣ አር.ኤስ) ጋር በመተባበር የህፃናት ካታራክት አይን ማዕከልን በኢትዮጵያ ውስጥ አቋቁመዋል። ሜርሲ ኬር ኢንተርናሽናል የሚባል አሜሪካ የሚገኝ ድርጅት መስራችና ዋና ስራ አስፈፃሚ ናቸው።

ኘሮፌሰር ባደግ የብርሀን ኢንተርናሽናል ባንክ መስራችና የቦርድ አባል ሲሆኑ፣ የካናዳ እና አሜሪካ ኢ.ኤ.ሲ.ኤ. ቦርድ አባል፣ ሲ.አር.ዲ.ኤ. ዩ.ኤስ.ኤ. የቦርድ አባል እና በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን ፖስተሮች ፌሎውሺፕ ኘሬዝዳንት በመሆን አገልግለዋል። ኘሮፌሰር ባደግ የቢ.ኤ.ዲግሪ ከናይሮቢ ኬንያው ኢ.ኤ.ኤስ.ቲ፣ የኤም.ኤ. ዲግሪያቸውን አሜሪካ ሚዙሪ ስኘሪንግፊልድ ከሚገኘው ከኤ.ጂ.ጂ.ኤስ አግኝተዋል። በዩኤስኤ ካሊፎርኒያ ከሚገኘው አዙሣ ፓስፊክ ዩኒቨርሲቲ ማስተር ኦፍ ዲቪኒቲ እና የዶክትሬት ዲግሪ አግኝተዋል።



አቶ ደረጀ በላይ

የዳሎል አይል አ.ማ. ተባባሪ አደራጅ እና የቦርድ አባል

አቶ ደረጀ በላይ የዳሎል አይል አ.ማ. መስራች አባል እና ተባባሪ አደራጅ ናቸው፡፡ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በንግድ አስተዳደር ዲፕሎማ ከዩኒቲ ዩኒቨርሲት ኮሌጅ አግኝተዋል። አቶ ደረጀ ወጣት ኢንተርፕሬነር ሲሆኑ ከለጋ ዕድሜያቸው ጀምረው የትራንስፓርትና የመሳሰሉት ሌሎች በርካታ የቤተሰቦቻቸው የንግድ ሥራዎችን በበላይነት በማካሄድ ላይ የቆዩ ሲሆኑ በዘርፎቹም ጥልቅ የሆነ የሥራ ልምድ አዳብረዋል። በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በምትገኘው ሀሙሲት ከተማ የሚገኝ የነዳጅ ማደያ ጣቢያ ባለቤት ሲሆኑ በዚህ ሥራ ላይ የነዳጅ ማደያ ጣቢያ አሰራር እና አመራርን በተመለከተ ሰፊ ልምድ አዳብረዋል። የሼል ኢትዮጵያ ሊሚትድ የሚሰጠውን አገልግሎት በከፊል ለኮቢል እስከሸጠበት ጊዜ ድረስ አቶ ደረጀ ለሼል ኢትዮጵያ አገልግሎቶችን በማደያቸው አማካኝነት ይሰጡ ነበር። በአሁኑ ጊዜ አቶ ደረጀ የሎጅ ግንባታ፣ የሪል ኢስቴት እና እርሻ የመሳሰሉ የተለያዩ ስኬታማ የንግድ ሥራዎችን በማካሄድ ላይ ይገኛሉ። አቶ ደረጀ የኢትዮጵያ አስጎብኚዎች ማህበር መስራች አባል ናቸው። በማስጎብኘት ስራ ዘርፍ በቀዳሚነቱና በስኬታማነቱ የሚታወቀው የኢትዮ-ደር ትራቭል ኤጀንሲ ባለቤትም ናቸው።



## ስለ አደራጆች መግለጫ



አቶ ገብረአምላክ ገ/ጊዮርጊስ
የዳሎል አይል አ.ማ. ተባባሪ አደራጅ እና የቦርደ ፀሃፊ

አቶ ገብረአምላክ ገ/ጊዮርጊስ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ፋክልቲ በ1990 ዓ.ም. ተመርቀው በኢትዮጵያ መድን ጅርጅት በነገረፈጅነት ለአንድ አመት ከሰሩ በኋላ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የህግ ፋክልቲ በህግ በመምህርነት አገልግለዋል። ለአንድ አመት ካስተማሩ በኋላ ኖርዌይ ወደ ሚገኘው ኦስሎ ዩኒቨርሲቲ የህግ ፋክልቲ ኖርዌጅያን ሴንተር ፎር ሂዩማን ራይትስ ውስጥ የማስትሬት ዲግሪ ትምህርት ተከታትለዋል። ወደ ሀገራቸው ተመልሰው እስከ 1996 ድረስ በኮሌጁ ውስጥ በማስተማር በማማከር፣ በህግ ጥናት እና በልዩ ልዩ አስተዳደራዊ ስራዎች አገልግለዋል። በ1997 ዓ.ም. ካሊፎርኒያ ፣ሣን ፍራንሲስኮ ከሚገኘው የሣንፍራንሲስኮ ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት በኢንተርናሽናል ትራንዛክሽንስ ኤንድ ኮምፓራቲቭ ሎው የማስትሬት ዲግሪ አግኝተዋል። ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ በጠበቃነትና በህግ አማካሪነት በመስራት ላይ ይገኛሉ። በተለያዩ የህግ ርዕሰ ጉዳዩች ላይ ጥናት ያደረጉ ሲሆን በተለያዩ የመንግስት እና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ስልጠናዎችን ሰጥተዋል። በፋና ኤፍ ኤም 98.1 ዘወትር ሰኞ ከ2፡30-3፡30 "ስነ- ህግ" በሚል በህግ እና ፍትህ ነክ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚቀርበው ቀጥታ የሬዲዮ ወግ ፕሮግራም አዘጋጅና አቅራቢም ናቸው። የዳሎል አይል አ.ማ. የህግ አማካሪ እና ተባባሪ አደራጅ ናቸው።

# የኢትዮጵያ የነዳጅ ኢንዱስትሪ አጭር ቅኝት

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የነዳጅ ምርቶችን ሙሉ በሙሉ የምታስመጣ ሀገር ነች። የነጭ እና ጥቁር ነዳጅ ምርቶች በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት (ኢነድ) አማካኝነት በሦስተኛ ወገን አቅራቢዎች ወደ ሀገር ውስጥ ይገባል። የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ምርቶቹን ከአቅራቢዎች ተረክቦ ጅቡቲ በሚገኘው ሆራይዘን ተርሚናል ማከማቻ ቦታ ላይ በማከማቸት የተለያየ ደረጃ ያላቸውን እነዚህን ምርቶች ማለትም ቤንዚን፣ ናፍታ፣ ነጭ ጋዝ፣ ቀላል የነዳጅ ዘይት፣ ከባድ የነዳጅ ዘይት፣ እና የጄት/የአውሮፕላን/ ነዳጅ ዘይትን መንግስት በተመነው የትርፍ ስሌት መሠረት ለነዳጅ ኩባንያዎች ያከፋፍላል። በተጨማሪም የኢ.ነ.ድ. ቤንዚን ከሱዳን ያስመጣል። የአዲስ አበባ ከተማ የቤንዚን አቅርቦትን በተመለከተ መንግስት ናይል ፔትሮሊየም ከተባለ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚሰራ የሱዳን ኩባንያ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ኩባንያው ቤንዚንን ከኢታኖል (ኢ-5) ጋር ሱሉልታ በሚገኘው የነዳጅ ማከማቻ እየቀላቀለ ኢ-5ን ለነዳጅ ኩባንያዎች ያከፋፍላል።

መንግስት የነዳጅ ዋጋዎችን የሚቆጣጠር ሲሆን የነዳጅ ዋጋ በየወሩ በመከለስ ላይ ይገኛል። የነዳጅ ዘይቶችና ቅባቶች ግን በነዳጅ ኩባንያዎቹ አማካኝነት ከውጭ ሀገር በቀጥታ የሚገቡ ሲሆን የመሸጫ ዋጋቸውን መንግስት በየሩብ ዓመቱ ይወሰናል። መንግስት ለነዳጅ ዘይቶች እና ቅባቶች የሚተምነው የትርፍ መጠን ለነዳጅ ምርቶች ከሚተመነው አነስተኛ ትርፍ ጋር ሲነፃፀር ጠቀም ያለ ነው።

እ.ኤ.አ. በ2008 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አመታዊ የነዳጅ ፍጆታ ከ2 ቢሊዮን ሊትር በላይ ነበር። በዚሁ ዓመት ሀገር አቀፍ የነዳጅ ዘይቶችና ቅባቶች ፍጆታ ከ25 ሚሊዮን ሊትር በላይ ይገኛል። የነዳጅ እና የነዳጅ ዘይቶችና ቅባቶች ፍጆታ በየዓመቱ 10% እየጨመረ ሲሆን ይህም የዕድገት አቅጣጫ ለሚቀጥሉት ዓመታት እንደሚቀጥል ይገመታል። እየጨመረ በመሄድ ላይ ያለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ መንግስት በመሠረተ ልማት፣ሀይል፣ማዕድን ፍለጋ እና ሌሎች ዘርፎች የሚያደርገው እንቅስቃሴ የነዳጅ ምርቶች አቅርቦት ፍላጎት የበለጠ እንዲጨምር አድርገውታል።

ለረጅም ዓመታት እየጨመረ የሚሄደውን የነዳጅ ምርቶች ፍላጎት ለማርካት አነስተኛ ውድድር ብቻ ያደርጉ የነበሩ አለማቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች የነዳጅ ኢንዱስትሪውን ተቆጣጥረውት ነበር። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሼል፣ ሞቢል፣ ቶታል እና አጂፕ በኢትዮጵያ ውስጥ የነዳጅ ምርቶችን በማከፋፈል ላይ የተሰማሩ ብቸኛ ኩባንያዎች ነበሩ። እነዚህ ኩባንያዎች የሚከተሉዋቸው ዓለም አቀፍ ስትራቴጂዎች በነዳጅ ዘይት እና ጋዝ ፍለጋ ላይ የሚያተኩሩ በመሆኑ እና ኩባንያዎቹ በሚከተሉዋቸው እጅግ ጥብቅ የሆኑ የደህንነት መመዘኛዎች (safety) አማካኝነት በአፍሪካ ውስጥ ከሚያከናውኑዋቸው የነዳጅ ማሰራጨት ስራዎች ለመውጣት ተገደዋል። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ጥቂት ኩባንያዎች በነዳጅ ሥራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ኢትዮጵያ ያሉዋት የነዳጅ ኩባንያዎች ቁጥር አነስተኛ ሲሆን የንግድ ውድድሩም በጣም አናሣ ነው። ለማነፃፀርያ ያህል በኡጋንዳና ኬንያ በነዳጅ ምርቶች ማከፋፈል ላይ የተሰማሩ በመሀከላቸው ከፍተኛ የሆነ የንግድ ውድድር ያላቸው ከ50 በላይ ኩባንያዎች ይገኛሉ።

የነዳጅ ምርቶች ፍላጎት በቀጣይነት እያደገ ቢሆንም በነዳጅ ኩባንያዎች በኩል ያለው የመስፋፋት (ተጨማሪ ማደያዎች በመገንባት ረገድ) እና አቅርቦት ግን በቂ አይደለም። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ አለም አቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች ሀገራችንን የመልቀቃቸው ሁኔታ የነዳጅ ኢንዱስትሪው እየጨመረ በመሄድ ላይ ያለውን የነዳጅ ፍላጎት የማሟላት አቅሙን አዳክሞታል። አሁን እየታየ ካለው የኢኮኖሚ ዕድገትና መንግስት በመሠረተ ልማት፣ የሀይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች፣ ማዕድን በማውጣትና በሌሎች ዘርፎች በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ለማፍሰስ ካለው ዕቅድ አኳያ ሲታይ በአሁኑ ወቅት በነዳጅ ዘርፍ በፍላጐትና በአቅርቦት መካከል የሚታየው በእጅጉ የሰፋ ነው።

ኢትዮጵያ በማዕድን ኢነርጂ በኩል ዕምቅ ሀብት አላት ተብሎ ይታመናል። በሀገራችን በአሁኑ ወቅት በሀይድሮ ኤሌክትሪክ ፓወር ፕሮጀክቶች እና የነዳጅ እና ጋዝ ፍለጋ በኩል የሚደረጉ ጥረቶች የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋል በመንግስት በኩል ቁርጠኝነት መኖሩን የሚያመለክቱ ጉልህ ምስክሮች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የነዳጅ ማከፋፈል ሥራ ከሚያስገኘው ጠቀም ያለና አስትማማኝ ትርፍ ባሻገር ሀገር በቀል የነዳጅ ኩባንያዎችን ዓቅም መገንባት ለወደፊቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረ ሀብትና ዕውቀት ከፍተኛ ትርፍ ወደሚያስገኘው የጋዝና ነዳጅ ፍለጋ ሥራ የመሸጋገሪያ ድንጋይ በመሆን ያገለግላል።

## ስለ ዳሎል አይል አ.ማ. አጭር መግለጫ

ዳሉል አይል አ.ማ. በልዩ ሁኔታ ኢትዮጵያዊ የሆነ ከታች የተዘረዘሩትን የሚያሟላ የነዳጅ ድርጅትን ለማቋቋም ቆርጠው በተነሱ ኢትዮጵያውን ሞያተኞች የተመሰረተ ነው፤

- ዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው
- በአንድ የማደያ ጣቢያ የተለያዩ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በማቅረብ ደንበኞች በነዳጅ ማደያ ጣቢያ የሚያገኙትን አገልግሎት አዲስ መልክ ማስያዝ
- ከተለመደው የንግድ አሰራር ልቆ እና ርቆ በመሄድ አዳዲስ የንግድ መንገዶችን በመከተል የደንበኞችን ምቾት መጨመር

ራዕይ

በኢትዮጵያ እጅግ ተመራጭ የነዳጅ ኩባንያ መሆን

ዓላማ

አመቺ፣ ቅልጥፍና የተምላበት እና ልዩ በሆነ አገልግሎት ጥራት ያላቸው ነዳጆችን፣ ቅባቶችንና ሌሎች ተያያዥ ምርቶችን አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለደንበኞች ማቅረብ፤

የኩባንያው ምርቶች

ዳሎል አይል አ.ማ. የሚሰማራባቸው የንግድ ሥራዎች ዓይነት በተመለከተ የክፍለ ሥራ /ፌዝ/ አካሄድን ይከተላል። ሥራ በሚጀምርባቸው የመጀመሪያዎቹ ሶስት ዓመታት በዋናነት በሚከተሉት ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል።

- የነዳጅ ምርቶች:- ቤንዚን፣ናፍታ እና ነጭ ጋዝ
- የነዳጅ ቅባቶችና ዘይቶች
- ሌላ ተያያዥ ምርቶች እና አገልግሎቶች (ነዳጅ ነክ ያልሆኑ)

ኩባንያው ገበያውን ከተቆናጠጠ ከኋላ የሁለተኛ ዙር የአክስዮን ሽያጭ ለህዝብ ያቀርባል። በአራተኛው የሥራ ዘመኑ ኩባንያው የሚያቀርባቸው ምርቶችና አገልግሎቱን በማስፋት የሚከተሉት እንዲካተቱ ያደርጋል።

- ቢቱሜን (የአስፋልት ሬንጅ)
- የአውሮፕላን ነዳጅ (አቪዬሽን ጋዝ እና ጄት ኤ-1)
- ኤልፒጂ (ቡታ ጋዝ)

የዳሎል አይል አክስዮን ማህበር እና የአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚገኙበት ቦታ

የዳሎል አይል አ.ማ. ዋና መስሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል። ኩባንያው ሥራ ከሚጀምርበት ጊዜ አንስቶ በ5 ዓመታት ውስጥ አነስተኛ የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ በሚገኝ ቦታ ይገነባል። ኩባንያው የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎች የሚገነቡባቸውን ስትራቴጂያዊ ከተሞችን እና አካባቢዎችን በጥንቃቄ አጥንቷል። እንደ እስትራቴጂ ዳሎል አይል ለባለሞተር ተሽከርካሪዎች አመቺና ተደራሽ በሆኑ ከፍተኛ የሆነ የትራፊክ ፍሰት ባለባቸው የንግድ ቦታዎችና አካባቢዎች በተገቢው ሁኔታ ኢንቬስት ለማድረግ ትኩረት ያደርጋል። ከተለመደው በነዳጅ ማደያዎች አማካኝነት አገልግሎት የመስጠት አሰራር በተጨማሪ ኩባንያው ወደ ተጠቃሚዎች ቀረብ ተብሎ አገልግሎት የሚሰጥባቸው አዳዲስ እና ልዩ የአገልግሎት አሰጣጥ መንገዶችን ተግባራዊ ያደርጋል።

## በዳሎል አይል አ.ማ. ላይ ኢንቬስት የሚያደርጉባቸው አምስት ምክንያቶች፣

**1**

**የነዳጅ ዘርፍ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ትርፍን የሚያስገኝ በመሆኑ:-** ነዳጅ በአለም ላይ በከፍተኛ ደረጃ ከሚሸጡ ምርቶች አንዱ ነው። ከሌሎች የንግድ ሥራዎች በተለይ የነዳጅ ኩባንያዎች አመሰራረት/አወቃቀር አገልግሎት ለመጀመር የሚያስፈልገውን የመነሻ ሥራ ሰፊ የሆነ አማራጮችን የሚሰጥ ነው። የዳሎል አይል አ.ማ. አላማ የአክስዮን ሽያጩን በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ወዲያውኑ የነዳጅ ማደያ ጣብያዎችን ግንባታ በመጀመር በስድስት ወራት ለማጠናቀቅ ነው። መስከረም 2003 ዓ.ም. ሥራውን በይፋ የሚጀምርበት ጊዜ ይሆናል።

በኢትዮጵያ መንግስት ለነዳጅ ዘይቶች እና ቅባቶች የተተመነው የትርፍ መጠን ለነዳጅ ምርቶች ከተተመነው አነስተኛ ትርፍ ጋር ሲነፃፀር ዳጐስ ያለ ነው። ቢቱሜን፣ የአውሮፕላን ነዳጅ እና ቡታጋዝም ማራኪ የሆነ ትርፍ ያስገኛሉ። ከፍ ብለው ከተጠቀሱት የነዳጅን በማከፋፈል ከሚገኙ ትርፎች በተጨማሪ ዳሎል አይል አ.ማ. በመላ ሀገሪቱ በሚገነቡ ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቁ የነዳጅ ማደያ ጣብያዎች ላይ ነዳጅ ነክ ያልሆኑ የንግድ ስራዎችን ለማካሄድ በትጋት ይንቀሣቀሣል።

<u>የዳሎል አይል አ.ማ. የወደፊት ገቢ ማሣያ</u>

<u>እ.ኤ.አ. ከ2011 እስከ 2016 ላለው ጊዜ</u>

| ዓይነት | መግለጫ | ዓመታት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 |
| ካፒታል ኢንቨስትመንት | (‘000) ብር | 150,000 | | | 100,000 | | |
| | | | | | | | |
| የኔትዎርክ ዕቅድ | የማደያ ጣብያዎች ብዛት - የኩባንያው የሆኑ | 20 | 20 | 20 | 30 | 30 | 30 |
| | የማደያ ጣብያዎች ብዛት - የአዳዮች የሆኑ | 10 | 20 | 30 | 40 | 50 | 50 |
| | የማደያ ጣብያዎች ብዛት ድምር | 30 | 40 | 50 | 70 | 80 | 80 |
| | | | | | | | |
| የሽያጭ መጠን | የኢንዱስትሪው መጠን ግምት(‘000) ሊትር | 3,218,070 | 3,606,602 | 4,209,410 | 4,563,875 | 5,153,161 | 5,153,161 |
| | የገበያ ድርሻ - ዳሎል አይል አ.ማ. | 6% | 9% | 14% | 18% | 21% | 21% |
| | የሚገመት ሽያጭ - ዳሎል አይል አ.ማ. | 201,209 | 341,740 | 589,701 | 820,243 | 1,067,572 | 1,067,572 |
| | | | | | | | |
| የሽያጭ ገቢ | ድምር ትርፍ (‘000) ብር | 36,039 | 57,039 | 100,887 | 132,871 | 188,231 | 188,231 |
| | ተጓዳኝ ገቢ(‘000) ብር | 1,920 | 2,112 | 2,429 | 2,915 | 3,643 | 3,643 |
| | ጠቅላላ ገቢ (‘000) ብር | 37,959 | 59,151 | 103,316 | 135,785 | 191,874 | 191,874 |
| | | | | | | | |
| ወጪ | የማከማቻ እና ተያያዥ ስራዎች ወጪዎች(‘000) ብር | (1,373) | (1,510) | (1,737) | (2,084) | (2,605) | (2,605) |
| | የሽያጭ ቦታዎች ወጪ(‘000) ብር | (638) | (743) | (931) | (1,248) | (1,789) | (1,789) |
| | የገበያና ሽያጭ ወጪዎች (‘000) ብር | (8,475) | (9,322) | (10,721) | (12,865) | (16,081) | (16,081) |
| | የጋራ የድጋፍ አገልግሎቶች (‘000) ብር | (4,517) | (4,968) | (5,714) | (6,857) | (8,571) | (8,571) |
| | ዲፕሪሽየሽን (‘000) ብር | (6,796) | (6,796) | (6,796) | (13,811) | (13,811) | (13,811) |
| | ጠቅላላ ወጪዎች (‘000) ብር | (21,798) | (23,341) | (25,898) | (36,864) | (42,857) | (42,857) |
| ታክስ ሣይከፈል የተጣራ ገቢ | | 16,161 | 35,810 | 77,418 | 98,921 | 149,017 | 149,017 |
| | ታክስ - 30% | 4,848 | 10,743 | 23,226 | 29,676 | 44,705 | 44,705 |
| ታክስ ተከፍሎ የተጣራ ገቢ | | 11,313 | 25,067 | 54,193 | 69,245 | 104,312 | 104,312 |

ማስታወሻ - ዳሎል አይል አ.ማ. ከሶስት ስኬታማ የስራ አመታት በኃላ ካፒታሉን በተጨማሪ 100 ሚሊዮን ብር ለማሳደግ አቅዷል።

2

ለነዳጅ ምርቶች ያለው የፍላጎት መጠንና ባህርይ:- ነዳጅ በግዴታ የሚፈለግ ምርት ከመሆኑም በላይ ለነዳጅ ምርቶች ያለው ፍላጎት ቋሚ ነው። ተፈላጊነታቸው በዋጋ እና ሌላ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ከሚዋዥቀው ሌሎች የንግድ ሥራዎች በተለየ የነዳጅ ምርቶች ኢኮኖሚያዊ አድገት በሚቀንስበት ጊዜ እንኳን ተፈላጊነታቸው ይጨምራል። ለምሣሌ የሀገራችንን ሁኔታ እንኳ ብንመለከት ከጥር እስከ ሰኔ 2001 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ የነዳጅ ፍጆታ ባለፈው ዓመት ከነበረው ተመሣሣይ ጊዜ ጋር ሲነፃፀር በ7% ዕድገት አሣይቷል። ከኢንቨስትመንት አኳያም በዓለም በተፈጠረው የፋይናንስ ቀውስ በፈጠረው ጫና ምክንያት የበርካታ የንግድ ዘርፎች የሥራ እንቅስቃሴ የቀዘቀዘ ሲሆን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የነዳጅ ኩባንያዎች ጠቀም ያለ ትርፍ ማስገኘታቸውን በመቀጠላቸው ለባለሀብቶች አሁን የተፈጠረው የዓለም የፋይናንስ ቀውስ እንዲቋቋሙ የሚያስችል መተማመንን ፈጥረውላቸዋል።

3

የነዳጅ ንግድ ያለው የኪሣራ ስጋት አነስተኛ በመሆኑ:- በነዳጅ ንግድ ሥራ የነዳጅ አገልግሎት መስጫ ጣብያዎች መረብ አንድ ጊዜ ተገንብተው ሥራ ከጀመሩ በኋላ በካፒታል እሴቶች ላይ የሚደረገው ወጪ አነስተኛ ስለሚሆን በርከት ያለው የባለሀብቶች ገንዘብ የሚፈሰው እና የሚዘዋወረው የነዳጅ ምርቶች ግዥ ላይ ይሆናል። የተገዙ እና የተከማቹ ነዳጆች ከብር ቀጥለው በፍጥነት የሚለወጡ ሀብቶች በመሆናቸው በዘርፉ ላይ መሰማራት ባለሀብቶች የንግድ ሥራዎቻቸውን ዘርፈ ብዙ ለማድረግ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ መንግስት በሀገሪቱ የሚኖረውን የነዳጅ ምርቶች ስርጭት ቀና እንዲሆን በፈቀደው ማበረታቻ መሠረት የነዳጅ ኩባንያዎች ለ30 ቀናት ያህል በነዳጅ አቅርቦት ላይ ከኢ.ነ.ድ. የዱቤ አገልግሎት ይሰጣቸዋል። ከቁጥጥር አኳያም የወጪና የዋጋ አወጣጡ በከፍተኛ ሁኔታ ግልፅ እና አውቶማቲክ በመሆኑ የነዳጅ ንግድ ሥራ ለባለሀብቶች አስተማማኝ ነው። በንግድ ሥራው ላይ አንዳችም ክፍተት እንዳይፈጠር ለማድረግ ዳሎል ኦይል አ.ማ. አስፈላጊ በሆኑ የአሰራር ዘዴዎችና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ላይ ኢንቬስት ለማድረግ ዕቅድ አለው።

4

በዳሎል ኦይል አ.ማ. ኢንቨስት ያደረጉ ሁሉ  የሚያገኙት ነገር ይኖራል:-
አንድ መቶ እና ከዚያ በላይ የሆኑ አክስዮኖችን በመግዛት ሙሉ ክፍያውን እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም. ድረስ የሚያጠናቅቁ ባለአክስዮኖች ከሆኑ የዳሎል ኦይል አክስዮን ማህበር የነዳጅ ማደያና አገልግሎት መስጫ ጣብያ(Dealer) ወኪል ለመሆን ዕድል ይኖርዎታል፡፡ እርስዎ ራስዎ የሚያዙበት የነዳጅ ማደያ ጣብያን ለመምራት የሚያስችል ዕድል ለማግኘት ብቃት እና ፍላጎት አለዎት? መልስዎ አዎ ከሆነ ዳሎል ኦይል አ.ማ. ለርስዎ ይሆናል፡፡

ኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች በበዙበት ጊዜ ገንዘብዎን ለርስዎ እና ለቤተሰብዎ የፋይናንስ ዋስትና እና መረጋጋትን ሊያረጋግጥ በሚችል የንግድ ዘርፍ ላይ ለማዋል የሚፈልጉ ከሆነ ዳሎል ኦይል አ.ማ. ለርስዎ ተስማሚ ኢንቨስትመንት ነው፡፡ በመጨረሻም የዋጋ ግሽበቱ እና በእጅዎ ያለው የካፒታል መጠን የሚያሣስቦት ከሆነ ዳሎል ኦይል አ.ማ. እጅግ የላቀ የኢንቨስትመንት አማራጭዎ በመሆን እርስዎ በሌሎች የግል ጉዳዮችዎ ላይ እንዲያተኩሩ እድል ይሰጥዎታል፡፡

5

ዳሎል ኦልይ አ.ማ. አለም አቀፍ ደረጃ ያለው የሥራ አመራርን ተግባር ላይ ያውላል:-  ዳሎል ኦልይ አ.ማህበርን በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅግ ውጤታማ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ውስጥ የሚከተሉት ጠንካራ ጎኖቹ ይገኙበታል:-

- የኩባንያው መስራቾች ራዕይ ያላቸው እና ሼል እና ኤክሶን ሞቢል በመሳሰሉ ግዙፍ አለም አቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች ውስጥ የበለፀገ በሃገር ውስጥ እና አለም አቀፍ ቀጥተኛ የሥራ ልምድ ያላቸው  ናቸው፡፡
- የነዳጅ ዘይቶችንና ቅባቶችን በተመለከተ ዳሎል ኦይል አ.ማህበር ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያላቸው አለም አቀፍ ዘይቶችን ያቀርባል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ዳሎል ኦይል አ.ማ. በነዳጅ ንግድ ላይ ከተሰማሩ አለም አቀፍ ኩባንያዎች ጋር በሽርክና ወይም በጆይንት ቬንቸር በመስራት ተዋህዶ እና ተወዳደሪነትን ለመፍጠር ይሰራል፡፡
- ቁልፍ በሆኑ ስትራቴጂያዊ ቦታዎች ላይ በጥንቃቄ ኢንቨስት በማድረግ፣ እና ያሉንን የኔትዎርክ መገልገያዎች መቶ በመቶ በመጠቀም ኢንቨስመንታችንን በላቀ መልኩ ለማከናወን ኩባንያው ይጥራል፡፡
- የነዳጅ ምርቶችን በማቅረብ ላይ ብቻ በማተኮር አሰራራችን በተለመደው የነዳጅ ምርቶች ንግድ አሰራር አይገደብም፡፡ የዳሎል የነዳጅ ማደያ አገልገሎት መስጫ ጣብያዎች በላቀ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ፣ የተለያዩ ነዳጅ ነክ የልሆኑ ምርቶች እና አገልግሎቶች ለተጠቃሚዎች የሚያቀርቡ በአንድ ጊዜ ሁሉንም አገልግሎት የሚሰጡ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሀ
## ህግ ነክ መረጃዎች

### ምስረታ እና ምዝገባ

ዳሎል ኦይል አ.ማ. በኢትዮጵያ የንግድ ህግ መሠረት ተቋቁሞ ነሐሴ 22 ቀን 2001 ዓ.ም. በንግድ እና ኢንዱስሪ ሚኒስቴር ተመዝግቧል፡፡ ኩባንያው እያንዳንዳቸው የብር 1,000 ዋጋ ባላቸው አክሲዮኖች በብር 1,400,000 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ) መነሻ ካፒታል በ7 ግለሰቦች ተቋቁሟል፡፡ የሰባቱ መሥራች ግለሰቦች አጭር የማንነታቸው መግለጫ በዚህ ኘሮስቴክተስ ቀርቧል፡፡ አሁን በሚደረገው የአክስዮን ሽያጭ 150,000 አክስዮኖችን ለህዝብ በመሸጥ የኩባንያው ካፒታል ወደ ብር 151,400.000 ከፍ ይላል፡፡

### ኩባንያው ዓላማዎች

በመመስረቻ ፅሑፍ በተቀመጠው መሠረት ዳሎል ኦይል አ.ማ. የሚከተሉት የንግድ ዓላማዎች አሉት፡፡

1) የነዳጅ ምርቶችን ማሰራጨት
2) የነዳጅ ዘይቶችን እና ቅባቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትና ማስራጨት
3) የነዳጅ ማደያ ጣቢያዎችን አገልግሎት መስጠት
4) የነዳጅ ምርቶችን ማጓጓዝ
5) የነዳጅ ፍለጋና ማጣራት ሥራዎች ላይ መሰማራት
6) ከንግድ ዓላማው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሥራዎች ማከናወን

### አደረጃጀትና ስራ አመራር

የአመራር መዋቅር



አደራጃጀት

የኩባንያው የበላይ ውሣኔ ሰጪ አካል የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሲሆን የኩባንያው አሰራርን ለመከታተል ዓመታዊ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል። አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ የባለ አክስዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሊካሄድ ይችላል።

ባለ አክስዮኖች በመጀመሪያው አጠቃላይ ስብሰባቸው ላይ ለሦስት ዓመታት የሚያገለግሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ይመርጣሉ። የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ፓሊሲ ጉዳዮችን፣ ዓመታዊ ዕቅዶችን እና በጀትን የማፅደቅና የመከታተል እና የኩባንያውን ዋና ስራ አስፈፃሚ መሾምን በሚመለከት ሃላፊነት ይኖራቸዋል።

ሥራ አመራር

ዳሎል አይል አ.ማ. በአቶ ኢዲዲያ አሰፋ የሚመራ ጽ/ቤት አቋቁሟል።

የውጭ ኦዲተሮች

በባለ አክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይሾማሉ፤

## የትርፍ ክፍፍል

በንግድ ህጉ አንቀፅ 310 መሠረት ይህንን የአክስዮን አቅርቦት የሚቀበል አመልካች ከኩባንያው የተጣራ ትርፍ ውስጥ በዓመት 14 በመቶ (14%) ያህሉ ለሦስት ዓመታት ያህል ከላይ ለተጠቀሱት የኩባንያው አደራጆች እንዲከፈል በማይለወጥ ሁኔታ ስምምነት ውስጥ ገብቷል። ሰባቱም አደራጆች የማንነት መግለጫቸው በዚህ ፕሮስፔክተስ ውስጥ የተካተቱ ሲሆኑ የስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ. ባለቤቶች ናቸው። የኩባንያው የሥራ መጀመሪያ ቀን የነዳጅ ማደያ አልግሎት ጣቢያዎች ተገንብተው ኩባንያው በይፋ ስራውን የሚጀምርበት ቀን ነው።

## የፋይናንስ መረጃ

አሁን ያለበት ሁኔታ

የኩባንያው የማቋቋሚያ መነሻ ካፒታል በሰባቱ መስራቾች የተዋጣ ብር 1,400,000 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ) ሆኖ የእያንዳንዱ አክስዮን ዋጋ ብር 1,000 (አንድ ሺህ) ነው። እያንዳንዱ መስራች አባል የብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ) ካፒታል ኢንቨስትመንት አድርጓል። የኩባንያው ሙሉ ካፒታል የሚኖረው የአክስዮን ሽያጭ ሲጠናቀቅ ነው።

የባንክ ብድር

ኩባንያው በአሁኑ ጊዜ የባንክ ብድር የለበትም ነገር ግን ለስራ ማከናወኛ ካፒታል የሚሆን የኦቨር ድራፍት ብድር ከባንክ ሊያገኝ ይችላል።

የዲቪደንድ ፓሊሲ

እያንዳንዱ ባለ አክስዮን በአክስዮን ይዞታው ልክ ከኩባንያው የተጣራ ትርፍ ላይ ዲቪደንድ የማግኘት መብት ይኖረዋል። የሚከፈለው የዲቪደንድ መጠን በባለ አክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚገለፅ ይሆናል።

## የአክስዮን ሽያጭ

አክስዮን የሚገዙበት መንገድ

የአክስዮን ገዢዎች የፕሮስፔክተሱን ቅጂ ከአደራጆች ጽ/ቤት ወይም ከህጋዊ የሽያጭ ወኪሎች ማግኘት ይችላሉ። በውጭ ሀገር የሚኖሩ ገዢዎች www.daloloil.com ከሚለው ድህረ ገፅችን ፕሮስቴክተሱን ለማግኘት ይችላሉ። አክስዮኖች የሚሸጡት እ.ኤ.አ. ከነሃሴ 26 2001 እስከ ታህሣስ 22 2002 ድረስ ነው። ሁለት የማመልከቻ ቅፆች (አንድ ለግለሰብ አመልካቾች አንድ ለኮርፓሬት አመልካቾች) በዚህ ፕሮስፔክተስ በስተመጨረሻ ላይ ይገኛሉ። አክስዮን ገዢዎች ቅፆቹን ከአደራጆች ጽ/ቤት፣ ከህጋዊ ወኪሎች ወይም ከዳሎል አይል ድህረ ገፅ ማግኘት ይችላሉ።

የክፍያ ሁኔታ

የአንድ አክስዮን ዋጋ ብር 1,000 ሲሆን ለእያንዳንዱ አክስዮን ተጨማሪ ብር 70 የአገልግሎት ዋጋ ይከፈላል። የአክስዮን ክፍያ በዳሎል አይል አክስዮን ማህበር ስም ወደ ተከፈቱ ዝግ የባንክ ሂሣቦች የሚገባ ሲሆን የአገልግሎት ክፍያው በ “ስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ.” ስም ለዚሁ ዓላማ በተመሣሣይ ቅርንጫፎች በተከፈቱት ተንቀሣቃሽ

ሂሣቦች ገቢ ይደረጋል። የአክስዮን ክፍያው በዝግ ሂሣብ ውስጥ ተቀማጭ ሆኖ በባለ አክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ መሰረት ብቻ ይንቀሣቀሣል። የአገልግሎት ክፍያው ኩባንያውን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ የጥናትና ምርምር፣ የአስተዳደራዊ ወጪዎች፣ የሽያጭ ኮሚሽኖችን፣ የአማካሪዎች ክፍያ የመሳሰሉ የማስታወቂያ ወጪዎችን ለመሸፈን ይውላል። ክፍያዎችን በገጽ 3 በተጠቀሰው መልኩ በሙሉ ወይም በከፊል ማከናወን ይቻላል። የአገልግሎት ክፍያ ግዢው ሲከናወን በሙሉ በአንድ ጊዜ ይከፈላል። ክፍያዎችን በሙሉ በጽ/ቤታችን በአካል በመቅረብ ወይም በዚህ ፕሮስቴክተስ በተዘረዘሩት የባንክ ቅርንጫፎች መፈፀም ይቻላል። የአክስዮን ገዢዎች የባንክ የክፍያ ደረሰኝ ወደ ጽ/ቤቱ ወይም ህጋዊ ወኪሎች ዘንድ ማቅረብ አለባቸው። ያልተሟሉ ወይም የክፍያ ደረሰኝ ያልተያያዘባቸው ቅፆች ተቀባይነት አይኖራቸውም። የሽያጭ ወኪሎች ገንዘብ የመቀበል ስልጣን እንደሌላቸው አክሲዮን ገዢዎች ከወዲሁ እንዲያውቁት እናሳስባለን።

የባንክ የክፍያ ደረሰኝ እና የማረጋገጫ ደብዳቤው የአክስዮን ግዢ ማስረጃዎች በመሆናቸው ባለ አክስዮኖች ሙሉ ክፍያ አጠናቀው የአክስዮን ሰርተፊኬት እስከሚሰጣቸው ድረስ በጥንቃቄ ሊይዙዋቸው ይገባል። የአክስዮን ሰርተፊኬት የሚሰጠው የአክስዮን ግዢ ሙሉ ክፍያ ሲጠናቀቅ ብቻ ነው።

## <u>ክፍል ሰ</u>

## <u>ተጨማሪ መረጃዎች</u>

### <u>የመመስረቻ ፅሑፍ ማጠቃለያ</u>

የመመስረቻ ፅሑፍ 13 አንቀፆችን አሉት። ስለ ኩባንያው መቋቋም፣ ስለ መስራች አባላት፣ ስለ አክስዮን ማህበሩ የንግድ አላማዎች ይደነግጋል። የመመስረቻ ፅሑፋ ስለ ኩባንያው አካላት እና ስለ እያንዳንዳቸው ስልጣንና ሀላፊነት እንዲሁም ስለ ትርፍ አከፋፈል ይገልፃል።

<u>የመተዳደሪያ ደንቡ ማጠቃለያ</u>

የመመስረቻ ፅሑፋ ኩባንያው ሥራ የሚገዛበትን ስነ ስርዓት ይደነግጋል። ደንቡ 30 አንቀፆችን የያዘ ሲሆን የስብሰባ ጥሪ አደራረግ፣ስለ ምልዐተ ጉባኤ፣ ስለ ርቀት ድምፅ አሰጣጥ፣ ስለ ጠቅላላ ጉባኤ አብላጫ ድምፅ፣ የዋና ስራ አስፈፃሚ ስልጣንና ሀላፊነት፣ ስለኩባንያው የሂሣብ መዝገብ አያያዝና የፋይናንስ ሪፓርት አቀራረብ፣ ስለ አባልነት መልቀቅ እና የአባል መሞት የመሳሰሉት የስነ ስርዓትና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ይደነግጋል። በተጨማሪም አንድ የአክስዮን አይነት ብቻ ያለ መሆኑን እና ከአክስዮኖች ጋር ተያያዥ የሆኑ መብቶች እንዲሁም የባለ አክሲዮኖች መብትና ሀላፊነቶች በተመለከተም በዝርዝር ተደንግጓል።

<u>ባለቤትነት</u>

ባለቤትነት ሙሉ ክፍያ ከተፈፀመ በኃላ በሚሰጥ የአክስዮን ሰርተፊኬት ይረጋገጣል። እያንዳንዱ ባለአክስዮን የኩባንያውን ጉዳዮች በተመለከተ በጠቅላላ ጉባኤ በቀጥታ ድምፅ በመስጠት ወይም በዲሬክተሮች ቦርድ አማካኝነት ውሣኔ የመስጠት ስልጣን አለው።

<u>ይፋ የሆኑ ሰነዶች</u>

- የመመስረቻ ፅሑፍ
- የመተዳደሪያ ደንብ

## ሂሣብ የተከፈተባቸው ባንኮች ዝርዝር

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጎተራ ቅርንጫፍ

| | |
|---|---|
| ዳሎል ኦልይ ኢ.ማ. | |
| የዝግ ሂሣብ ቁ. | 0171843076100 |
| ስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ. | |
| ሂሣብ ቁ. | 0171843076200 |

- ሕብረት ባንክ ወሎ ሰፈር ቅርንጫፍ

| | |
|---|---|
| ዳሎል ኦልይ ኢ.ማ. | |
| የዝግ ሂሣብ ቁ. | 1161810704467018 |
| ስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ. | |
| ሂሣብ ቁ. | 1161810704567012 |

- ዳሽን ባንክ ቦሌ አካባቢ

| | |
|---|---|
| ዳሎል ኦልይ ኢ.ማ. | |
| የዝግ ሂሣብ ቁ. | 0012872988001 |
| ስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ. | |
| ሂሣብ ቁ. | 0012872987001 |

- ንብ ኢንተርናሽናን ባንክ ወሎ ሰፈር ቅ.

| | |
|---|---|
| ዳሎል ኦልይ ኢ.ማ. | |
| የዝግ ሂሣብ ቁ. | 147 |
| ስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ. | |
| ሂሣብ ቁ. | 146 |

- ወጋገን ባንክ ውሎ ሰፈር ቅርንጫፍ

| | |
|---|---|
| ዳሎል ኦልይ ኢ.ማ. | |
| የዝግ ሂሣብ ቁ. | 01 |
| ስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ. | |
| ሂሣብ ቁ. | 02 |

- አቢሲንያ ባንክ አሎምፐያ ቅርንጫፍ

| | |
|---|---|
| ዳሎል ኦልይ ኢ.ማ. | |
| የዝግ ሂሣብ ቁ. | 213 |
| ስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ. | |
| ሂሣብ ቁ. | 214 |

- ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ

| | |
|---|---|
| ዳሎል ኦልይ ኢ.ማ. | |
| የዝግ ሂሣብ ቁ.. | 175 |
| ስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ. | |
| ሂሣብ ቁ. | 174 |

- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ

| | |
|---|---|
| ዳሎል ኦልይ ኢ.ማ. | |
| የዝግ ሂሣብ ቁ. | 554866 |
| ስኬት ፕሮሞሽን ኋ.የተ.የግ.ማ. | |
| ሂሣብ ቁ. | 3450 |

# የግለሰቦች ወይም የኩባንያ/ ድርጅት ማመልከቻ

እኔ/እኛ ፤አቶ/ ወ/ሮ/ ካምፓኒ/ ድርጅት____________________

አድራሻ፡ ከተማ__________ ክ/ከታማ__________ ቀበሌ__________

የቤ.ቁ____________________ፖ.ሣ.ቁ__________

ስልክ፡- የሥራ ቦታ__________የቤት__________ ሞባይል__________

ፋክስ__________ ኢሜል __________

በዜግነት__________ የሆንኩ/የሆንን የዳሎል. ኦይል አክሲዮን ማህበር ተራ አክሲዮኖችን ከዚህ በታች በተዝረዘረው ሁኔታ ለመግዛት አመለክታለሁ/ እናመለክታለን፡፡

የእያንዳንዱ አክሲዮን ዋጋ ብር 1, 000/ አንድ ሺህ/ሆኖ ብዛታቸው__________/__________

የሆነ ተራ አክስኖች በድምሩ በብር__________/__________ለመግዛት እንደሚመለከተው ግዴታ ገብቻለሁ/ ገብተናል፡፡

ይህ ስምምነት እንደተፈረመ

1. ሙሉ ክፍያውን ማለትም ብር __________/__________ወይም (______%) ብር__________/__________ለዚሁ ጉዳይ ተብሉ በተከፈተዉ የዳሎል ኦይል አክስዮን ማህበር ዝግ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ አስገባለሁ/ እናስገባለን፡፡
2. ሁለተኛ ክፍያውን (______%) ብር__________/__________ በ __________ቀን እና
3. ቀሪውን (______%) ብር __________/__________ በ __________ቀን ለመክፈል ተስማምቻለሁ /ተስማምተናል፡፡

## የአገልግሎት ክፍያ

ለእያንዳንዱ የተገዛ አክሲዮን የሚከፈለው አገልግሎት ክፍያ 7 % ሲሆን ለተለያዩ የሽያጭና የስራ ማስኬጃ እንቅስቃሴዎች ክፍያ የሚውል ይሆናል፡፡ ጠቅላላ የአገልግሎት ክፍያ በአንድ ጊዜ ተሰልቶ ለዚሁ ጉዳይ ተብሎ በተከፈተው የስኬት ፐሮሞሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ አስገባለሁ/ እናስገባለን፡፡

የገንዘብ መጠን፡- የጠቅላላ አክሲዮን ብዛት __________x ብር 70.00, = __________

ለአክስዮን ሽያጭ በዳሎድ አክስዮን ማህበር አደራጆች የወጣውን መግለጫ/ prospectus/ በጥሞና ማንበቤን /ማንበባችንን እና የሽያጭ ሁኔታዎች ገደቦች እና ግዴታዎችን መቀበሌን/ መቀበላችንን አረጋግጣለሁ/ እናረጋግጣለን፡፡

ቀን __________

የአክሲዮን ገዢው ስም እና ፊርማ __________

የሽያጭ ወኪሉ ስምና ፊርማ __________

አ ድ ራ ሻ
ዳሎል አይል አክስዮን ማህበር
ፖ.ሣ.ቁ. 11937
ኢትዮ - ቻይና ወዳጅነት መንገድ (ወሎ ሰፈር)
ሜድኮ ባዮ ሜዲካል ኮሌጅ አጠገብ የሚገኘው አዲስ ህንፃ ሁለተኛ ፎቅ
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ስ.ቁ. + 25111 416 38 38 ፣ +2511 416 57 57
+ 25111 416 17 32 ፣ +2511 416 17 33
ፋክስ + 25111416 40 02
ኢ.ሜል፡- info@daloloil.com
ድህረ ገፅ፡- www. daloloil.com